Minnesota Department of Health • የባዮቴሮሪዝም መረጃ 10/8/2005

# ከቫይረስ የሚመጡ ብዙ ደም የሚያስፈስሱ ትኩሳቶች (VHFs)

## ከቫይረስ የሚመጡ ብዙ ደም የሚያስፈስሱ ትኩሳቶች ምንድን ናቸው?

ከቫይረስ የሚመጡ ብዙ ደም የሚያስፈስሱ ትኩሳቶች (VHFs) ከተለያዩ ቫይረሶች የሚመጡ የበሽታ ዓይነቶች ናቸው። እነዚህ በሽታዎች ብዙ የሰውነት ክፍሎችን በአንድ ጊዜ የሚጎዱ ናቸው። የደም ቧንቧዎችን ይጎዱና ሰዉነት እራሱን እንዳያስተካክል ያደርጉታል።



*የኢቦላ ቫይረስ*

አንዳንድ VHFs ቀላል ሲሆኑ ሌሎቹ ግን ለሞት የሚያደርሱ ሊሆኑ ይችላሉ። በአብዛኛው ጊዜ የደም መፍሰስንና ሌሎች ምልክቶችን ያስከትላሉ። የደም መፍሰሱ ለብቻው ሞትን አያመጣም።

እንደ ጦር መሣሪያ ሊጠቀሙባቸው የሚቻሉ የ VHF ቫይረሶች አሉ። እነሱም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- ኢቦላ
- ማርበርግ
- ላሳ
- ኒው ወርልድ አሪናቫይረሶች
- ማቹፖ (የቦሊቪያ ብዙ ደም የሚያስፈስስ ትኩሳት)
- ጁኒን (የአርጀንቲኒያ ብዙ ደም የሚያስፈስስ ትኩሳት)
- ጉዋናሪቶ (የቬኔዙዌላ ብዙ ደም የሚያስፈስስ ትኩሳት
- ሳቢያ (የብራዚል ብዙ ደም የሚያስፈስስ ትኩሳት)
- የስምጥ ሸለቆ ትኩሳት
- ቢጫ ወባ
- የኪያሳኑር ፎረስት በሽታ ቫይረስ
- ኦምስክ ብዙ ደም የሚያስፈስስ ትኩሳት

## እነዚህ በሽቶች የሚይዙት እንዴት ነው?

በተፈጥሮ ሰው VHF የሚይዘው ከተበከሉ ቁንጫዎች፣ ቢንቢዎች ወይም አይጠ መጎጦች ነው። ከአይጠ መጎጥ ከሚመጣ ሽንት፣ ሠገራ ወይም ሌላ ነገር በመንካት ሊይዝ አይችልም። ሰው ከቢንቢ ወይም ከቁንጫ ንክሻ ወይም የተበከለን ቁንጫ ከመጨፍለቅ VHF ሊይዘው ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ግን ሰዎች እንዴት ሊይዛቸው እንደቻለ ለማውቅ አስቸጋሪ ይሆናል።

## እነዚህ በሽታዎች ከሌላ ሰው ሊይዙ ይችላሉ?

አንዳንድ የVHF ቫይረሶች -ኢቦላን፣ ማርበርግንና ላሳን ጨምሮ - ከሰው ወደ ሰው ሊተላለፉ ይችላሉ። ሰውን በቅርብ ከመገናኘት ወይም በሰውነት ፈሳሽ በኩል ይተላለፋሉ። ከተበከሉ ዕቃዎች ለምሳሌ እንደ መርፌና ሲሪንጅ ሰው ሊይዘው ይችላል።

## እነዚህ በሽታዎች እንደ መሣሪያ ሊጠቀሙባቸው ይቻላል ተብሎ የሚታሰበው ለምንድን ነው?

አንዳንድ የ VHF ቫይረሶች -ኢቦላን፣ ማርበርግን፣ ላሳን፣ ቢጫ ወባንና አንዳንድ የኒው ወርልድ አሪናቫይረሶችን ጨምሮ - በፈሳሽ መልክ መዘጋጀት ይችላሉ። ከዛም አየር ላይ ተበትነው ሰውን ለመበከል ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ሌሎች VHF ደግሞ -የስምጥ ሸለቆ ትኩሳትን ጨምሮ- የሙከራ ቤት ውስጥ አየር ላይ ሲለቀቁ በሽታን አስከትለዋል።

የቀድሞው ሶቪዬት ዩኒየን የማርበርግ ቫይረስን እንደ መሣሪያ ተጠቅመውበታል እንዲሁም ኢቦላ፣

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH
Communications Office
625 North Robert Street/Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-4989
www.health.state.mn.us

# ከቫይረስ የሚመጡ ብዙ ደም የሚያስፈስሱ ትኩሳቶች - ገጽ 2

ላሳ፣ የስምጥ ሸለቆ ትኩሳት፣ ቢጫ ወባና ኒው ወርልድ አሪናቫይረሶች ላይ ሙከራ አካሂደዋል። አሜሪካን አገር ከማርበርግና ከኢቦላ በስተቀር ሁሉም ቫይረሶች ላይ ጥናት አድርጓል። ሰሜን ኮሪያ የቢጫ ወባን እንደ ጦር መሣሪያ ለመጠቀም ሰርቶታል ተብሎ ይታመናል።

## VHF ሊታከም ይችላል?

አንዳንድ VHF ጸረ ቫይረስ መድሃኒቶችን በመጠቀም ማከም ይቻላል። ለነዚህ በሽታዎች ባጠቃላይ የምልክቶች ሕክምናና ጥንቃቄ ያስፈልጋል።

## ከእነዚህ በሽታዎች መከላከል ይቻላል?

ለአንዳንድ VHFs (ቢጫ ወባን ጨምሮ) የሚሆኑ ክትባቶች አሉ። ለሌሎቹ የ VHF ቫይረሶች የሚሆን ክትባት በጥናት ላይ ነው። እነዚህ በሽታዎች በተፈጥሮ የሚገኙባቸው ቦታዎች ውስጥ ቢንቢዎችንና ቁንጫዎችን ለመቆጣጠር የሚወሰዱ እርምጃዎች ከተወሰኑ ዓይነት VHF ለመከላከል ይረዳል።

## ለ VHF የተጋለጥኩ ከመሰለኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

ለ VHF ተጋልጠው ከሆነ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። ሆኖም ሐሳብ ከያዝዎት ዶክተርዎን ያነጋግሩ። በአካባቢዎ ጥርጣሬ የሚያሳድር እንቅስቃሴ ካዩ - ማለትም የበሽታውን ጀርሞች እንደ ጦር መሣሪያ ለመጠቀም የሚሞክር ካዩ - በአካባቢዎ ለሚገኘው የሕግ አስከባሪ ድርጅት ያሳውቁ።